# የኢህአዴግ ልዑካ በሰሜን አሜሪካ የኢንቨስትመንት ጥሪና በኢትዮጵያ የነጋዴው ስቃይ

ነጻነት ጀቤሳ

የኢህአዴግ ልዑካን የፊታችን ሚያዚያ 10 እና 11/2011 በአሜሪካና አውሮፓ ከተሞች በውጭ ከሚኖረው ኢትዮጵያዊ ጋር ለመምከር እንደሚመጡ በይፋ አስታውቀዋል፤የተልእኮው ኣላማ ብዙ ዝርዝር ቢቀርብበትም ያልተገለጸው ዋናው አላማው በሰሜን አፍሪካና በአረቡ ኣላም የቀጠለው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ እውን እንዲሆን ዲያስፖራው የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ለማምከን እንዲሁም ወደሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ በስፋት እንዲፈስ ለማድረግ ያለመ ነው፤

በእርግጥ ኢትዮጵያውያን ከዚህ ቀደምም በሀገር ቤት ገብተው ኢንቨስት እንዲያደርጉ ተጠይቀዋል፤ውጤቱ ደግሞ ምን እንደነበር ወዳጆቻችን እና ጉዋደኞቻችን በከፍተኛ ጥረት ያፈሩትን የውጭ ምንዛሪ በሰበብ አስባቡ ተነጥቀው ሲመለሱ አንዳንዶቻችን አይተናል፤ሌሎቻችንም ሰምተናል፤የተሸለ ነገር አልመው ሄደው የሰበሰቡትን ተዘርፈው ሕይወታቸው ሲመሳቀል ታዝበናል፤ያልተመለሱትም ብሶታቸውን ለራሳቸው ለመንግስት ባለስልጣናት በአደባባይ በተደጋጋሚ ገልጸው ሰሚ ማጣታቸውን ሲናገሩ አድምጠናል፤ወይንም የተናገሩት ተጽፎ አንብበናል፤ ባሰለፍነው ጥር ወር የሆነውም ለዚህ አባባላችን ማረጋገጫ ነው።ከውጭ ወደ ሀገር ቤት ለኢንቨስትመንት የሄዱ ወገኖች በሀገሪቱ ፍትህ አለመኖሩን ፣ መልካም አስተዳደር እንደሌለ ለራሳቸው ለመንግስት ባለስልጣናት በአደባባይ የተናገሩትን New business Ethiopia በተባለው ጋዜጣ ላይ ታትሞ ወጥቷል፤ዘገባውን በሚከተለው ሊንክ ማየት ይቻላል።

http://newbusinessethiopia.com/index.php?option=com_content&view=article&id=399:ethiopian-diaspora-complain-about-good-governance-&catid=38:government&Itemid=38

ጥር 13/2003 በአዲስ አበባ በሼራተን አዲስ የውጭ ጉዳይ ሚንስትሩ ሃይለማርያም ደሳለኝ እና ሌሎች የመንግስት ባለስልጣናት ለኢንቨስትመንት ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ ኢትዮጵያዊያን ዲያስፖራዎች ጋር ዛሬ ኤክስፖርት ያደረጉትን አጀንዳ ይዘው በተወያዩበት ወቅት የገጠማቸው ቅሬታ ፣ተቃውሞና ቁጣ ነበር፤በውይይቱ ወቅት ከዲያስፖራው ባለሃብቶች የቀረቡ ቅሬታዎች በከፊል ቀጥለው ተመልክተዋል፤

መንግስት በመጪዎቹ 5 አመታት ስራ ላይ ላማዋል ላቀደው የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ ተግባራዊነት የራሳቸውን አስተዋጽኦ ለማድረግ ተዘጋጅተው እንደነበሩ የገለፁ ከሳዑዲ አረቢያ የተመለሱ ዲያስፖራ "በሀገሪቱ ፍትህ የለም፤ ከፈለጋችሁ ይህንን በዝርዝር ልንነግራችሁ እችላለሁ" በማለት ቅሬታቸውን ገልፀዋል። "ያለፍትህና መልካም አስተዳደር ብቃት ያለው ሰራተኛ በቀበሌና በወረዳ ደረጃ ካልተፈጠረ መንግስት የፈለገውን ማራኪ ነገር ቢያቅድም ተግባራዊ ሊሆን አይችልም" ሲሉ ሌላ አስተያየት ሰጪ ተደምጠዋል፤ ም/ጠ/ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በመሆን ባለፈው መስከረም ወር የተሾሙት አቶ ሀ/ማርያም ደሳለኝ በመሩት በዚህ ስብሰባ ላይ ሌላ ተሰብሳቢ ደግሞ አድሉ ሲሠጣቸው

"ለምን እንደሰበሰባችሁን ማወቅ እፈልጋለሁ? ስለ ሀገራችን የሚሰማንን ለመስማት እና ከዚያ ወደየቤታችሁ ለመሄድ ነው? ወይስ መፍትሄ ልትሰጡ? ይህ ከሆነ እንደገና ስንገናኝ በነዚህ

**ችግሮች ላይ አናወራም ማለት ነው፤" ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። የግል ባንኮች ለግብርናው ዘርፍ የበለጠ የባንክ ብድረር ለመስጠት ፈቃደኛ ባልሆኑበት ሁኔታ ውስጥ የ5 አመቱን የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ** እንዴት **ማሳካት ይቻላል? የሚል ጥያቄም ከተሰብሳቢዎቹ ተነስቷል ላለፉት 18 ወራት የባንክ ብድር ለማግኘት ያደረጉት ሙከራ አለመሳካቱም በአንድ ተሰብሳቢ** ተወስቷል።

**በውጭ ሀገር የሚመረቱ መድሃኒቶችን ሀገር ውስጥ ለማምረት ከውጭ ማሽን ያስገቡ በውጭ የሚኖሩ ባለሀብት ከአዲስ አበባ አስተዳደር መሬት ለማግኘት የደረሰባቸውን ችግር ዘርዝረዋል።ከዚሁ ከህክምና ጋር በተያያዘ ሌላ ተሰብሳቢም ላለፉት ሦስት አመታት ሕይወትን ለማዳን ለሀገሪቱ ትልቅ ጠቀሜታ ያለው መድሃኒት ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ባደረጉት ሙከራ የመድሃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር መስሪያ ቤት 70 በመቶውን እንዳገደባቸው ገልፀዋል። "እጅግ ጠቃሚ እና ፈዋሽ የሆኑ መድሀኒቶች እንዳይገቡ መከልከላቸው ይደንቀኛል" ሲሉ ግርምታቸውን አሰምተዋል።** *(ሙሉውን የእንግሊዘኛ ዘገባ በላይኛው ሊንክ ማግኘት ይቻላል)* **በሀገሪቱ ያለው ሁኔታ ለዲያስፖራውን ምቹ አለመሆኑን ለስርዓቱ ቅርብ በሆነው ሪፖርተር ጋዜጣ ላይ በቀልድ መልክ የቀረበው ቁም ነገር** *በቀጣዩ ሊንክመመልከት ይቻላል*

http://www.ethiopianreporter.com/index.php?option=com_content&view=article&id=5455:2011-03-23-07-06-04&catid=104:2009-11-13-13-46-39&Itemid=624

እንኩዋን ከውጭ ሀገር የሄደው ኢትዮጵያዊ ቀርቶ በሀገር ቤት በንግዱ ዓለም ዘመናት ያስቆጠሩ በሰበብ አስባብ እየተገፉ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በገዢው ፓርቲ ኩባንያዎች እና በጥቂት ሸሪኮቻቸው እጅ ወድቋል፤ ባለሀብቱ በግብር፣በአራጣ ወዘተ እየተሳበበ ወደ ወህኒ እየተነዳ፣ የቀረውም እየኮበለለ ይገኛል፤ጥቂት ማይባሉትም ወደ ድህነት ተገፍተዋል፤ጥቂቶችም ራሳቸውን አጥፍተዋል፤የጌታነህ ትሬዲንግ ባለቤት አቶ ዮሃንስ ጌታነህና የአሴ ማርብል ባለቤት አቶ አስፋው ይርጋ በዚህ ረገድ ተጠቃሽ ሰለባዎች ናቸው፤ (ስለነዚህ ሙዋቾች በዚህ ሊንክ ያገኛሉ) http://allafrica.com/stories/200812230640.html

በሀገሪቱ ያለው የንግድ እነቅስቃሴና የነጋዴው ሁኔታ በውጥረት የተሞላ ስለመሆኑ የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ አያሌው ዘገየ የሰጡትን መግለጫ በሚከተለው ሊንክ ማግኘት ይቻላል http://www.ethiopianreporter.com/index.php?option=com_content&view=article&id=4134:2010-11-21-09-09-48&catid=102:2009-11-13-13-46-03&Itemid=623

ነጋዴው በሀገሪቱ በሰፈነው የጉልበት አገዛዝ ስጋት ውስጥ በመውደቁ የህልውናው ዋስትና አድርጎ የወሰደው በስልጣን ላይ ላሉት ገዢዎች እጅ መንሻ ማቅረብ ነው። ስልጠን ላይ ያለው ቡድን አንድ ግዜ ለምርጫ ዘመቻ፣ሌላ ግዜ ደግሞ ለህንጻ ማሰሪያ በሚል የንግዱን ሕብረተሰብ እያስገበረ ይገኛል፤ ኢሕአዴግ ለ2002 ምርጫ ብቻ 57 ሚሊዮን ብር ከነጋዴው ሰብስቧል፤በዚህ መልክ ነጋዴውን እያራቆተ እስካለፈው ጥቅምት ከወጪ ቀሪ 100.3 ሚሊዮን ብር ማከማቸቱን በይፋ አስታውቋል፤ነጋዴዎቹ ለኢሕአዴግ በአንድ ግዜ እስከ 600 ሺህ ብር እና ከዚያ በላይ እንደሚያዋጡ ይርጋ ሓይሌ የተባሉትን ታዋቂ ነጋዴ እንደ አብነት መውሰድ ይቻላል፤እኚህ ሰው ለኢህአዴግ ምርጫ 630 ሺህ ብር አዋጥተዋል።

የእኚህ ግለሰብ ኩባንያ ከመስቀል አደባባይ እስከ ቦሌ አለም ዓለም ዐቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ያለውን የ4.1 ኪሎሜትር መንገድ ስራ በጨረታ ካሸነፈ በሁዋላ ተከልክሉዋል፤ ባለሃብቱ እርዳታውን የሰጡት ከክልከላው በሁዋላ በመሆኑ ነጋዴው ምን ያህል በፍርሃት ውስጥ እንዳለ አመልካች ነው፤በሀገሪቱ በሪል ስቴት መስክ ቀዳሚ የሆነው የሃያት ሪል ስቴት ባለቤትን ጨምሮ ቁጥራቸው የበዛ ነጋዴዎች በእስር ቤት ናቸው፤ ለእስር የሚሰጠው ምክንያት ታክስ፣ አራጣ የሚል ቢሆንም ፣ በኩባንያዎቻቸው የገዢው መደብ ሰዎችን ባለድርሻ እንዲያደርጉ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚመጣባቸውን ጥሪ ባለማስተናገድ እነደሆነም የንግዱ ማህበረሰብ አባላት ሰፈር የሚነሳ ጉዳይ ነው፤በቅርቡ በአዲስ አበባ በሕገ ወጥ ተግባር ውስጥ ተገኝተዋል በተባሉ ሪል ስቴቶች ላይ በተወሰደ ርምጃ አንዳንዶችን ለማሰር ሌሎችን በይቅርታ ለማለፍ መንግስት መወሰኑን ጠ/ሚ/ሩ በአደባባይ መናገራቸው የሚያሳው የሕግ የበላይነት ጥሰትን ብቻ ሳይሆን ያልገበሩ ዜጎች ዕጣ ፋንታ ምን እንደሆነ ጭምር ነው። ( ነጋዴዎች ለኢሕአዴግ ገንዘብ ማዋጣታቸውን በሚከተሉት ሊንኮች ማግኘት ይችላሉ)

http://www.capitalethiopia.com/index.php?option=com_content&view=article&id=12781:business-leaders-swell-eprdf-coffers&catid=12:local-news&Itemid=4

http://www.addisfortune.com/Vol%2010%20No%20540%20Archive/Adama%20Raises%20Funds%20for%20EPRDF%20Congress.htm

http://www.ethiopiainsight.com/news/funds_to_finance_eprdf_hqs.htm

ዲያስፖራው የግል መኖሪያ ቤት እንዲሰራ እየተጠየቀ አንዳንዶች ሄደው መስራት የ ቻሉ ቢሆንም ፣በከተማዋ ዳር ከሰሩት ውጭ ሌሎቹ ለሰሩት ቤት ዋስትና አጥተው ከፍተኛ አደጋ ላይ ወድቀዋል፤ቦሌ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ኦሎምፒያ አካባቢ እንዲፈርሱ የተወሰነባቸው ቤቶች ለዚህ እንደአብነት ይወሰዳሉ፤እነዚህ እንዲፈርሱ

የተወሰነባቸውና ባለፈው ህዳር ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው ቤቶች ደረጃቸው ከፍ ያለ ብቻ ሳይሆን ፣አንዳንዶቹ የግንባታ ፈቃድ ወስደው በቅርቡ ተሰርተው የተጠናቀቁና በመጠናቀቅ ላይ የነበሩ ናቸው፤ጥቂት የማይባሉት ቤቶች ዋጋቸው ከ 5 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመቱ እና የዚምባቤ ኤምባሲን ጨምሮ የውጭ መንግስታትና ድርጅቶች የተከራዩዋቸው .ቤቶች ናቸው እንዲፈርሱ የተወሰነባቸው። በከተማዋ ዳር የሰሩትም ቢሆኑ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ንብረታቸውን ለመሸጥ ለመለወጥ ቢፈልጉ እንኳዋን 80 በመቶ ሰርተው ካላጠናቀቁ መሸጥ እንዳይችሉ ሕገ መንግስቱ የሰጠው የንበረት ባለቤትነት መብት ተሽሮ በህግ ታግደዋል፤። *ዝርዝር ሪፖርት በሚለከተለው ሊንክ ማግኘት ይችላሉ*

http://www.capitalethiopia.com/index.php?option=com_content&view=article&id=13886%3Aresidents-cry-foul-as-modern-homes-face-forced-demolition-&Itemid=9

http://www.addisfortune.com/Vol_10_No_555_Archive/agenda.htm

http://www.capitalethiopia.com/index.php?option=com_content&view=article&id=13712:all-homes-opposite-mega-building-to-be-demolished-&catid=12:local-news&Itemid=4

ከተማዋን እንለውጣለን በሚል በጥንት እና በደከሙ ቤቶች ላይ በተወሰደው ርምጃ በበጎ የተመለከቱት ጥቂቶች አልነበሩም፤ሆኖም በሚፈርሱት ቤቶች ምትክ የሚሰራው ኮንዲሚኒየም ደረጃው እጅግ የወረደ በመሆኑ የከተማውን ውበት በዘላቂነት ይጎዳል ከሚለው የስነ-ሕንጻ ባለሙያዎች ስጋት ባሻገር፣ እነዚሁ ቤቶች በስመ ዕጣ በተደራጀ መልኩ ከገዢው ፓርቲ ጋር ቅርበት ላላቸው ወገኖች እየተሰጠ ነው፤በማካካሻነት ለቤት ባለቤቶች የሚሰጠው ገንዘብ እንኳዋን ቤት ሊሰራ መሰረት ለማውጣት እንኳዋን የማይበቃ ነው፤ዜጎች በዚህ ረገድ ጮህው ሰሚ አጥተዋል፤ዛሬ በኢትዮጵያ ቐዋሚው ብቻ ሳይሆን ሙታን ጭምር እየተፈናቀሉ መሆኑን በአዲስ አበባው ቅዱስ ዮሴፍ ቤተክርስቲያን የተፈጸመው በቂ ምስክር ነው። ..

አቶ ስብሃት ነጋ በአደባባይ ለቪኦኤ የአማርኛው አገልግሎት ተናግረው እናዳረጋገጡት ዛሬ በኢትዮጵያ ትልቁ ኩባንያ

የሕወሃቱ ኤፈርት ነው፤ርሳቸው በትግሉ ዘመን በሰበሰብነው ሀብት ተነሳን ብለው ቢናገሩም ያለምንም መያዣ 1.7 ቢሊዮን ብር ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ወስደዋል፤ወለዱ ብቻው ወደ 300 ሚሊዮን ብር ሲጠጋ ፋይሉ እንዲዘጋና እንዲጠፋ ተደርጉዋል፤የባንኩ ፕሬዚዳንት የነበሩት አቶ ገዛሀኝ ይልማ በ1998 (በኢትዮጵያ አቆጣጠር) ራሳቸውን ያጠፉበት ን ሁኔታ የቅርብ ምንጮች ከዚህ የኤፈርት ብድር ጋር ያይዙታል፤ቀደም ሲል ከሀገሪቱ ባንክ የወሰዱትና ያስቀሩት ገንዘብ አልበቃ ብሎአቸው ዛሬም በተጨማሪ እየወሰዱ ለፓርቲያቸው ሬዲዮ ፋና እና ለዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል ሕንጻ ገንብተዋል፤ሌሎች በርካታ ሕንጻዎችም ደርድረዋል፤ በተከራይ በኩል ያለውን ችግር ለመቅረፍ የመንግስት ተቋማት የነበሩበትን የመንግስት ቤት እየለቀቁ ወደ እነሱ ሕንጻዎች እንዲገቡ አድርገዋል።

ዛሬ በንግድና ኢንቨስትመንት መስክ ያለው ዕውነታ ከዚህም እጅግ የሰፋ በሙስና የተበከለ፤ ከሀብት እና ችሎታም ባሻገር ታማኝነትንና በይበልጥም የደም መመዘኛን በዋናነት የሚጠይቅ በመሆኑ ሕሊናን በመሸጥ እንኩዋን የሀገር ባለድርሻ መሆን አይቻልም፤ …በአጠቃላይ ሀገራችን በኢኮኖሚው መስክ ብቻ ሳይሆን በፖለቲካውም መስክ አፈና የነገሰባት፣የሚሊዮኖች ድምጽ የታፈነባት የጨለማ ምድር ሆናለች ፤ሀገራችንን ጭለማ ውስጥ ከተው፣ሕዝብ አደህይተው እና አራቁተው የተዘፈዘፉብንን ሽክሞች በህዝባዊ እንቅቃሴ ለመጥረግ የተላኩብንን የጭለማ መልክተኞች በማሳፈር በሀገር ቤት ላለው ወገናችን ብርታት እንሁነው፤ ዘረኝነት ይብቃ !.አምባገነንነት ይብቃ ! ዘረፋ ይብቃ !.ድንቁርናም ይብቃ !

ሚያዚያ 2003/April 2011